# የተኩላው እረኛ

ይግረማችሁ አለን ፤ ተኩላ ቤተ ሰሪ
ጅብና ቀበሮ ፤ ሆነው አጋፋሪ
ጭልፊትና አሞራ ፤ መልዕክቱን አብሳሪ
እባብና ጊንጡ ፤ ደናሽና አዝማሪ
እንግዳ ተጋባዥ ፤ በግ ሆነች ተጠሪ
እንዲህ ነው ጀግንነት ፤ ካጠለቁ ሱሪ
አስመስሎ መቅረብ ፤ መሆን ነው መሰሪ ።

ቢመጣ ጭንጋፉ ፤ ቢተካም አህያ
የሚመረጥ የለው ፤ እንዳለ ፋንድያ
ዛሬም አድሮ ቃሪያ ፤ ተግባር የለው ሞያ
ጥንት የምናውቃቸው ፤ የጠባብ መለያ
በረቱ ተሞላ ፤ በጉፋያ ርያ
ጀግኖችሽ የት ገቡ ፤ ያባቶች አርአያ
አልነጋ አለ ሌቱ ፤ ዛሬም በኢትዮጵያ ።

አገር ለመበተን ፤ ያመቻቹ መንገድ
በጎጥና መንደር ፤ በቋንቋ ሲነገድ
በናት አገሩ ላይ ፤ እሳት ጭሮ ሲያነድ
እሱም ላይቀርለት ፤ በተራው ሊሳደድ
የባንዳው ወያኔ ፤ ዛሬ እንዲህ ሊዋረድ
ምናለ ፈጣሪ ፤ ቢወርድና ቢፈርድ
ቢያሳየን በቁሙ ፤ ሲገባ እሳት ሲነድ
ከነ ልጅ ልጆቹ ፤ ጥቁር ውሻ ይውለድ ።

በህልም የመሰለኝ ፤ ለካስ ነበር በውኔ
ማመን ተስኖኛል ፤ ያየሁትን ባይኔ
ሰንደቋን አሳዩን ፤ ያዲሷን ፊንፊኔ
ልለምን ወይ ዛሬ ፤ እድሜ ለወያኔ
ለባንዳ ልጅ ባንዳ ፤ ለዚያ ላረመኔ
ለአረብ ምንደኛ ፤ ልክስክስ ምስለኔ
ቃል አጠረኝ እኔስ ፤ ለፍርድ ለብያኔ ።

በጥላቻ ጦዘው ፤ ያለልክ ያበዱ
አገርና ሕዝብን ፤ እጅግ ያዋረዱ
ደም እየሸቀጡ ፤ ደም እየነገዱ
ባገር ያላገጡ ፤ ባገር የቀለዱ
በስተመጨረሻ ፤ ቢወርዱም ከዘውዱ
መሰሉ ተተካ ፤ እነሱ ሲሄዱ
ያሁኑ ይባስ መጡ ፤ በሜንጫ የሚያርዱ ።

አንዱ ባለ ሜንጫ ፤ አንደኛው ተጋሩ
እራያን ሸንሽነው ፤ ሁሉም ተደመሩ

ወሰንተኛ ሆነው ፤ መስመር አሰመሩ
ቀንሶ መደመር ፤ ይባላል ባጭሩ
ግራ ለገባቸው ፤ ለተደናገሩ
የዛሬ መቶ ዓመት ፤ ሳይውሉ ሳያድሩ
ማብራሪያ ይሰጣሉ ፤ ጠ/ሚኒስትሩ ።

ኢትዮጵያዊ መባል ፤ ክብርና ዋጋቸው
በራስ መተማመን ፤ ያልፈጠረባቸው
እንደ ትላንትናው ፤ ዛሬም ያልገባቸው
የአማርኛ ጠላት ፤ ላቲን አምላካቸው
ተረት ተረት ሰምተው ፤ የሚቀላ አይናቸው
ከወያኔ አያንሱም ፤ በቂም ጥላቻቸው
ቁርሾ ሰንቀዋል ፤ የት ይሆን ጥጋቸው
ቃላት አይደልለን ፤ አይግዛን አፋቸው ።

ሃያ ሰባት አመት ፤ እንዲያ እንዳልማሰነ
በመደመር ሂሳብ ፤ ሁሉም መረቀነ
ድካም ከንቱ ቀረ ፤ በባዶ መከነ
በአፍዝ አደንግዝ ፤ ሕዝብ ተጨፈነ
አገር ያንቀላፋል ፤ ዛሬም አልባነነ
የጨመተው ተኩላ ፤ በግ እረኛ ሆነ
ሜንጫ ይዘው ገብተው ፤ መሰለው የዳነ
የተኩላው እረኛ ፤ እውነትም ጀገነ ።

የጨመተው ተኩላ ፤ ከታጨ ለእረኛ
የዱር አራዊቶች ፤ ሆነው እድምተኛ
እንቅልፍ አልወስድ አለኝ ፤ እንዴትስ ልተኛ
እነሱን እያየሁ ፤ አልሆን በሽተኛ
መራቅ ነው ምርጫዬ ፤ መሆን ስደተኛ
ፈጣሪ በቃ እስኪል ፤ ፊቱ እስኪዞር ለኛ ።

ታዛቢው

August 9, 2018